# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

ፕሮግራም:- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ግንቦት 25 ቀን 2004 ዓ.ም**

**የውጭ ሀገር ጋዜጠኛው በፌዴራል ፖሊስ ተደብድቦ ለሁለት ቀናት ታሰረ፤**

**አንዲት ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኛም አብራው ታስረ ነበር፤**

**የኦህዴዱ ሙክታር ከድር ከስልጣኑ ተባረረ፤**

**መለስ ስልጣኔን እለቃለሁ ብሎ አሁንም በህዝቡ ላይ ተሳለቀ፤**

በእብሪት እና በትዕቢት የተወጠረው የወያኔ አምባገነን ቡድን መሪ መለስ ዜናዊ በቡድን 8 አባል ሀገራት ስብሰባ ላይ የውርደት ካባ ተከናንቦ ከተመለሰ ወዲህ በሀገር ውስጥ የደህንነት ቁጥጥሩ በጠበቀ ሁኔታ እየተሰራ መሆኑን ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ የደረሰን ጥቆማ ገለፀ::

መለስ በካምፕ ዴቪድ የደረሰበትን ውርደት ተከትሎ በሀገር ውስጥ የደህንነት ክትትሉ በታዋቂ ባለሀብቶች እና ዲያስፖራዎች ላይ የጠነከረ ከመሆኑም በተጨማሪ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይም እጅግ ጠንካራ ክትትል በማድረግ ላይ እንደሚገኝ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ይገልፃሉ::

ሰሞኑን ይሄንኑ የደህንነት ጥብቅ ክትትል ተከትሎ የሙስሊሙን ማህበረሰብ ብሶት ለመዘገብ ወደ መስጊድ ተጉዞ የነበረውን በኢትዮጵያ የአሜሪካ ድመጽ የእንግሊዝኛው ወኪል በሆነው ፒተር ሀይንላይን ላይ የወያኔ ደህንነቶች እና የፌዴራል ፖሊሶች በወሰዱት የማፈን እርምጃ ለሁለት ቀናት ታስሮ መፈታቱ ታውቆዋል::

ዓርብ ግንቦት 17 ቀን 2004 ዓ.ም የሙስሊሙ ማህበረሰብ እንደ ወትሮው ግዜ ሁሉ በየመስጊዱ ተገኝቶ የሶላት ስነስርዓት አድርጎ ከጨረሰ በሁዋላ በወያኔ ላይ ተቃውሞ እያሰማ በነበረበት ወቅት በቦታው ተገኝቶ ሁኔታውን ተከታትሎ ለመዘገብ ጥረት ሲያደርግ የነበረው ፒተር ሀይን ላይን የተባለው ጋዜጠኛ በደህንነቶች ታፍኖ ተወስዶ በፌዴራል ፖሊሶች ሲደበደብ ማደሩን የማዕከላዊ ምርመራ ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ገልጾዋል:: ከጋዜጠኛው ጋር በአስተርጉዋሚነት ሰትስራ የነበረችው ስመኘሽ የተሰኘችው ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኛም አብራ ታፍና ለእስር ተዳርጋ እንደነበር ከማዕከላዊ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ለማረጋገጥ ተችሎዋል:: ጋዜጠኛው በደረሰበት ድብደባ

EthioLion.Com

እራሱን እንደሳተና ሌሊት በድንጋጤ ራስ ደስታ ሆስፒታል ለህክምና ብለው እንደወሰዱትም ከውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል::

የአሜሪካ ድምጽ ጋዜጠኛ እና ጋዜጠኛ ስመኝሽ አስኮ መንገድ ላይ በሚገኝ ምድር ቤት ውስጥ ታስረው በብሔራዊ መረጃና ደህንነት ከፍተኛ ባለስልጣን በሆነው ጌታቸው በሚባለው ግለሰብ ለሁለት ሰዓታት የፈጀ ምርመራ ሲደረግባቸው እንደቆየ የጠቆሙት ምንጮቹ በተለይ ፒተር በመቅረጸ ድምጹ ቀርጾት የነበረውን የሙስሊሙ ህዝብ ተቃውሞና መግለጫ ካሴት ቀምተው እንደወሰዱበትም ታውቆዋል::

ዛሬ በመላ ሀገሪቱ የወያኔ ቡድን በሚያደርሰው ግፍ እና በደል በመበሳጨት የሙስሊሙ ህዝብ የግፍ አገዛዝ በቃን ሰለቸን.......ወያኔ ዘረኛ ቡድን ነው......በእምነት ጣልቃ እየገባ እየፈተፈተ ነው ...... በማለት በየቦታው ተቃውሞ እያሰሙ መሆኑን ለመዘገብ በቦታው ተገኝቶ የነበረው ጋዜጠኛ ፒተር በደህንነቶች እንግልት እና ወከባ አልፎ ተርፎ ድብደባ እንደተፈጸመበት የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ቢያውቁም የወሰዱት እርምጃ እንደሌለ ለማወቅ ተችሏል::

የመለስ ዜናዊ ቅርብ የሆነው በረከት ስምኦን ሳይቀር ጋዜጠኞቹ መያዛቸውን ሪፖርት ተደርጎለት እንደነበር የጠቆሙት ምንጮቹ በአግባቡ ተይዘው ወደ ማረፊያ ክፍል ከመውሰድ ይልቅ በምድር ቤት ውስጥ ለሁለት ሰዓታት ያህል ምርመራ ሲደረግባቸውና በተለይ በፒተር ላይ ድብደባ ሲፈጸምበት እንደቆየ በረከት አሳምሮ እንደሚያውቅ የጠቆሙት ምንጮቹ የቀረጻቸው ካሴቶች እንዲቀሙ ያዘዘውም እሱ መሆኑን አብራርተዋል::

በጋዜጠኛው ላይ የደረሰው ጉዳት ከባድ በመሆኑ ከሌሊቱ 7 ሰዓት ላይ ወደ ራስ ደስታ ሆስፒታል ተወስዶ ማደንዘዣ እና ማስታገሻ መርፌ የተወጋ ቢሆንም ድብደባው እና ህመሙ ከባድ ስለነበር በማግስቱ በድጋሚ ወደ ዚያው ሆስፒታል ተወስዶ ህክምና ሲሰጠው እንደነበረም ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል::

ለሁለት ቀናት ማዕከላዊ እስር ቤት ታስሮ የተፈታው ጋዜጠኛ ፒተር እነ ጋዜጠኛ ስመኝሽ ለይ አቃቤ ህግ ክስ እንዲመሰርት እነ በረከት ስመኦን መመሪያና ትዕዛዝ ቢሰጡም ሊያስከስሰቸው የሚችል በቂ ምክንያት በለማገኘቱ ክሱ ውድቅ የተደረገ ሲሆን የደረሰበትን መከራና ግፍ ለየትኛውም ሚዲያ ቢገልጽ በ24 ሰዓት ከሀገር እንደሚባረር ስለተነገረው ድብደባውንና የደረሰበትን ግፍ ሁሉ ተሸክሞ ሊያስቀር እንደቻለም ምንጮቹ አስረድተዋል::

ለማስተርጎም አብራው የነበረችው ጋዜጠኛ ስመኝሽ ላይም ደህንነቶቹ እና የፌዴራል ፖሊሶቹ አዛዦች በሚያስደነግጥ ሁኔታ ሆድዋን በእርግጫ ሲቀጠቅጡዋት እንደነበር የጠቆሙት ምንጮቹ የደረሰባትን ችግር ለየትኛውም ሰው እንዳትናገር ጭምር ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣትም ከምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል::

በተያያዘ ዜና ከሙስለሙ ማህበረሰብ ጋር ቅርብ ቁርኝት አላቸው ......በስውር ድጋፍ ያደርጋሉ ተብለው በመለስ ዜናዊ ተጠርጥረው ልዩ ክትትል ሲደረግባቸው ከነበሩት የወያኔ ከፍተኛ

EthioLion.Com

ባለስልጣን መሀከል የኢህአዴግ ጽህፈት ቤት ኃላፊ የነበረው ሙክታር ከድር ከቦታው ተነስቶ ለግዜው እረፍት እንዲወጣ መደረጉ ታወቀ::

መለስ ዜናዊ እንደ አይኑ ብሌን ሲሳሰት የነበረውና ከሁሉ አስበልጦ ሲንከባከበው የነበረው ሙክታር ከድርን ከሙስሊሙ ህዝብ ጋር ሊወግን ይችላል በሚል ከጽህፈት ቤት ኃላፊነት አንስቶ ቦዘኔ ያደረገው ሲሆን በምትኩ የመለስ ቀኝ እጅ ሬድዋን ሁሴን ቦታውን መያዙ ታውቆዋል::

የወያኔ ቡድንም በአሁኑ ሰዓት በውስጡ ምስቅልቅል እየደረሰበት ሲሆን በተለይ የኦህዴድ ሙስሊም ባለስልጣናት ላይ ልዩ ክትትሉ ተጠናክሮ መቀጠሉም እየተነገረ ይገኛል::

ለመለስ ቅርበት ነበረው የተባለው ይሄው የኦህዴዱ ከፍተኛ ባለስልጣን አባዱላ ገመዳ ከኦህዴድ ሊቀመንበርነት እና ከክልሉ ፕሬዝዳንትነት ሲነሳ ግምገማ ሲያደርግና የተፈጸመውን ሁሉ ክትትል እና ቁጥጥር እያደረገ ለመለስ ሪፖርት ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን ያስታወሱት ምንጮቹ በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርምና ዛሬ ተረኛ ሆኖ ስራ አጥ ቦዘኔ እንዲሆን መደረጉ መለስ ዜናዊ መጥጦ መጣል የተካነበት መሆኑን ያስረዳል ሲሉም የገዛ ባለስልጣናቱ እየተናገሩ ይገኛሉ::

ለግዜው በሁሉም ቦታ እየተገኘ የወያኔን እና የመለስን ጻድቅነት እየሰበከ የሚገኘው ሬድዋን ሁሴን የተባለው ከበረከት ስምኦን ባልተናነሰ ሁኔታ ከፍተኛ የተደራረበ ስልጣን ተሰጥቶት የሚገኝ ሲሆን ከበረሀ የመጡትም ሆነ አፍለኞችን እያሽከረከረ እንደሚገኝ ከምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል::

በአሁኑ ሰዓት በሚኒስትር ማዕረግ በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ የህዝብ አደረጃጀት ኃላፊና የኢህአዴግ ጽህፈት ቤት ኃላፊ የሆነው ሬድዋን ሁሴን በአሁኑ ወቅት ሙስሊሙ ህብረተሰብ ተቃውሞ በሚያቀርብበት አወሊያ ትምህርት ቤት ውስጥ ሲያስተምር የነበረ ሲሆን ዛሬ መልሶ ሙስሊሙን ማህበረሰብ ከመለስ ዜናዊ ባልተናነሰ ሁኔታ እያፈነና እያሰረ መገኘቱ አሳፋሪና አሳዛኝ በማለት ታዛቢዎች ይተቻሉ::

ከኦህዴድ ምክትል ሊቀመንበርነቱም ሳይሆን .....ከኢህአዴግ ጽህፈት ቤት ተጠሪነቱም ተባርሮ የሚገኘው ሙክታር ከድር ስራ ፈትቶ ለይምሰል ብቻ ቢሮ እየገባ እንዲወጣ መደረጉንም ምንጮቹ አክለው ገልጸዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ለ21 ዓመታት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እያናጠረ የሚገኘው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ሰሞኑን ስልጣኑን ከሶስት ዓመት በሁዋላ እንደሚለቅ መግለፁ ታወቀ::

በቅርቡ በአዲስ አበባ የዓለም ኢኮኖሚ ፎረም በተሰኘው ስብሰባ ላይ የተገኘው የሮያል አፍሪካ ሶሳይቲ ዳይሬክተር የሆነው ጋዜጠኛ ሪቻርድ ዳውደን ከመለስ ጋር ምስጢራዊ ውይይት ያደረገ ሲሆን ይሄንኑ አስመልክቶ ለህዝብ ይፋ ማድረጉ ታውቆዋል::


EthioLion.Com

ጋዜጠኛ ሪቻርድ እንደገለጸው ከሆነ የወያኔው ቡድን የስልጣን ዘመኑ የሚያበቃው እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር በ2007 በመሆኑ ያኔ መለስ ዜናዊም ስልጣኑን እንደሚለቅ ገለጾልኛል ካለ በሁዋላ በምትኩ ማን እንደሚሆን ፍንጭ አለመስጠቱንም አስረድቶዋል::

መለስ ዜናዊ በተለያየ ግዜ ከስልጠኔ እወርዳለሁ..... እለቃለሁ እያለ በተደጋጋሚ በመናገር የዋሆችን እየሸ ወደ መቆየቱ ግልፅ ሲሆን አሁንም ወቅቱ ሲደርስ እንደተለመደው ፓርቲዬ አስገደደኝ የሚል ምክንያት ለመስጠት መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው:: ሪቻርድ ከመለስ ጋር ቆይታ ባደረገበት ወቅት በአሁኑ ሰዓት በመከላከያ ውስጥ የህወሀት የበላይነት መንገሱን..... ዲሞክራሲ በሀገሪቱ አለመስፈኑን ያረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ከሶስት ዓመት በሁዋላ ስልጣኑን ለቅቆ ለሌላ እንደሚያስረክብ እንደገለጸለት ይፋ አድርጎዋል::

በህዝቦች ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተው ህገ መንግስት ቢጸድቅም በሀገሪቱ ያሉ ብሔረሰቦች በቁዋንቁዋቸው ብቻ እንዲናገሩ በርካታ ስራዎች ቢሰሩም የተዋጣለት ዴሞክራሲ መገንባት አልተቻለም ያለው መለስ ዜናዊ በህዝቡ ፈቃደኝነት ዘር..... ቀለም..... ቆዳ..... ቁዋንቁዋ..... ሳይለይ መላ የሀገሪቱ ዜጎች በፍቅር እና በመተሳሰብ እንዳሻቸው ሆነው በኖሩባት ሀገር ዘረኝነት እንዲነግስ እና ጥላቻ እንዲስፋፋ ያደረገ መሆኑ እየታወቀ በህዝቡ ፈቃደኝነት የተመሰረተ ህገ መንግስት ብሎ ማላገጡ የሚያሳዝን ነው ሲሉ ምሁራኖች እየገለጹ ይገኛል::

የሀገሪቱ የመከላከያ ሰራዊት አደረጃጀቱን አስመልክቶ ለተጠየቀው ሲናገር ተራ ወታደሮችን ለማመጣጠን እና ከሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ለማካተት ጥረት እየተደረገ ቢሆንም መከላከያን በበላይነት ሙሉ ለሙሉ የሚመራው ግን የህወሀት ቀድሞ ታጋዮች ብቻ እና ብቻ መሆናቸውን አምኖ መግለጹም ታውቆዋል::

በመከላከያ ውስጥ ዘረኝነት ነግሶዋል ፍትሀዊ የሆነ የስልጣንና የማዕረግ ድልድል ይደረግ ተብሎ ብዙ ግዜ ጥያቄ ቢቀርብም የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የአማራና የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ ከፍተኛ መኮንኖች ጨርሶ ከስራቸው ያባረራችወና አሊያም ሰበብ እየፈለገ ለእስር የዳረጋቸው ሲሆን በቅርቡም በስውር የማዕረግ እድገት የተሰጣቸው ጄኔራል ተብየዎች በሙሉ የህወሀት መኮንኖች መሆናቸው ተቁዋሙ በዘረኝነት የተወጠረ መሆኑን ያመላከተ ነው ሲሉም የሰራዊቱ አባሎች በብስጭት ይናገራሉ::

ባለፈው ወር ውስጥ ከ400 በላይ ከፍተኛ መኮንኖች የግዳጅ እረፍት እንዲወጡ በደብዳቤ የተገለጸላቸው ሲሆን እነኚሁ የሰራዊቱ አባሎች የአማራና የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ብቻ ሲሆኑ በምትኩ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ የህወሀት መኮንኖች ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን እንዲይዙ ተደርጓል::

በመጨረሻም በሰራዊት ብዛት እና በጦር መሳሪያ ኃይል ህዝቡን አፍኖ ያለው የወያኔ ቡድን አሁንም በከፍተኛ ወጪ የሰራዊት ምልመላ በማድረግ ላይ መሆኑ ታወቀ::

EthioLion.Com

ሰሞኑን ከአዲስ አበባ እና ከተለያዩ ገጠር ከተሞች የተመለመሉ ወጣቶች ለፌዴራል ፖሊስ አባልነት ተብለው ወደ ጦላይ የጦር ማሰልጠኛ ካምፕ እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን በየጦር ካምፖቹ ውስጥ ለ6 ወራት ሰልጥነው የነበሩ ከ30 ሺህ በላይ ወታደሮች እና የፌዴራል ፖሊሶች በአዲስ አበባና በተለያዩ ከተሞች ለጥበቃ በሚል መመደባቸው ታውቆዋል::

EthioLion.Com